# Übersetzungen der Dialoge

# የውይይቶች ትርጉም

**ምእራፍ 1**
**ይህ አንድ ዜማ ነው**

በዚህ በመጀመሪያው ምእራፍ ጀርመንኛ እንዴት እንደሚነገር የተለያዩ ምሳሌዎችን ታደምጣላችሁ። ይህ ደግሞ እያንዳንዱን ቃላት ለመረዳት ባይቻል እንኳዋ ቋንቋው ሲነገር የሚሰጠውን ድምጽ ለመለየት ይጠቅማል። በመጀመሪያ ሁለት ሰዎች አርስበርስ ሲተዋወቁና ህጻናት የአሃዝ ጨዋታ ፈርዝ ሲደረድሩ ትሰማላችሁ። ከዚያም የራዲዮ ዜና ስርጭት፣ ቀጥሎም አንድ ዜማ፣ በመጨረሻም «ፋውስት» ከተሰኘው ከጎይተ ታዋቂ ድርሰት አንዲት ጥቅስ ታደምጣላችሁ። የመጨረሻዎቹ ሁለት ምሳሌዎች በሰፊው ይብራራሉ።

**Andreas:** ይህ አንድ ዜማ ነው
ይህ በክላውስ ሆፍማን የተደረሰ ዜማ ነው.
ይህ አንድ ጽሁፍ ነው
ይህ ጽሁፍ በጎይተ የተደረሰ ነው

**ምእራፍ 2**
**ሄላው ታክሲ!**

የዚህ ምእራፍ አላማ አንድን ባእድ ቋንቋ ለመረዳት የሚጠቅሙ ዘዴዎችን እንድታውቁ ማድረግ ነው። አንዳንዶቹ የጀርመንኛ ቃላት ምናልባት በአማርኛ ወይም በሌሎች ቋንቋዎች ከምታውቋቸው ቃላት ስለሚመሳሰሉ ትርጉማቸውን መገመት ትችሉ ይሆናል። የሚከተለው ድርጊት የሚፈጸመው በአደባባይ ነው። የሆቴል አውሮፓ ቋሚ እንግዳ የሆነው ዶር/ትሁርማን ታክሲ ይጣራል። ከዚያም ታክሲው ውስጥ ይሳፈርና ለታክሲ ነጂው (Taxifahrer) ወዴት ለመሄድ እንደሚፈልግ ይነግረዋል።

**Dr. Thürmann:** ሄላው ታክሲ!
**Taxifahrer:** ጤናይስጥልኝ
**Dr. Thürmann:** ጤናይስጥልኝ፣ እባክህ ሆቴል አውሮፓ ውሰደኝ
**Taxifahrer:** ሆቴል አውሮፓ፣ እሺ

**ምእራፍ 3**
**ሆቴል አውሮፓ**

በዚህ ምእራፍ የቋንቋ ኮርሳችን በአንድ ሆቴል ማለትም በሆቴል አውሮፓ እንደሚካሄድ ትረዳላችሁ። ከዚሁ በተጨማሪም የኮርሱን ታሪክ ባለሚናዎች ትተዋወቃላችሁ። የሆቴሉ ሃላፊ Frau Berger ስትሆን እንግዳ ተቀባዩ Andreas Schäfer እንዲሁም ክፍል አጽጂዋ Hanna Clasen ይባላሉ። ከዚያም የፈጠራ ምስላችን Ex እና የሆቴሉ ቋሚ እንግዳ Dr. Thürmann አሉ።

**አስተዋዋቂው** ይህ አቶ ሼፈር ነው - አንድሬያስ ሼፈር
ይህ ዶር/ትሁርማን ነው
ይህች ወሮ/በርገር ናት - ሊዛ በርገር
ይህች ሃና ናት - ሃና ክላዘን

ኢክስ ራስዋን ታስተዋውቃለች።
Ex: ሄላው! ሄላው! እዚህ ነኝ!

ኢክስ ለየት ባለ ዘይቤዋ የኮርሱን ዋና ዋና ባለሚናዎች ስም በድጋሚ ትናገራለች።
Ex: እኔና አንድሬያስ እና ወሮ/በርገር እና ሃና እና ዶር/ትሁርማን

አንድሬያስ በሆቴል አውሮፓ የእንግዳ መቀበያ ይገኛል።
Andreas: የእንግዳ መቀበያ! ሆቴል አውሮፓ፣ እንዴት አመሹ!

## ምእራፍ 4
## እርስዎ ማነዎት?

ዶር/ትሁርማን በሆቴል አውሮፓ ቋሚ እንግዳ ነው። ከዚያው እንደደረሰ የሆቴሉ ሃላፊ ወሮ/በርገር ሞቅ ያለ አቀባበል ታደርግለታለች።
Frau Berger: አሀ - ዶር/ትሁርማን! መልካም ምሽት ይሁንልዎ
Dr. Thürmann: እንዴት አመሹ
Frau Berger: አቶ ሼፈር፣ እኚህ ዶር/ትሁርማን ናቸው
Andreas: እንዴት አመሹ፣ ዶር/ትሁርማን
Ex: .... ምሽት!
Andreas: ዝም.... ኢክስ! ዝም!

ጥቂት ዘግየት በሎም ዶር/ትሁርማን አንድ ቢራ ወደ ክፍሉ እንዲወስድለት ለመጠየቅ ከእንግዳ መቀበያው ይደውላል። ዶር/ትሁርማን ጆሮው ደህና አድርጎ አይሰማም።
Andreas: የእንግዳ መቀበያ፣ እንዴት አመሹ!.
Dr. Thürmann: ማን ልበል?
Andreas: እንግዳ መቀበያ፣ሆቴል አውሮፓ
Dr. Thürmann: ምን አሉ? ማነው የሚናገረው?
Andreas: ሆቴል አውሮፓ፣ የእንግዳ መቀበያ
Dr. Thürmann: አሃ - አንድ ቢራ እፈልጋለሁ፣ አንድ ቢራ እባክህ
Andreas: አንድ ቢራ፣ እሺ! እና እርስዎ ማነዎት?

አንድሬያስ የዶር/ትሁርማንን ድምጽ ወዲያው ለይቶ ሊያውቅ አልቻለም። ይህ ደግሞ ዶር/ትሁርማንን በጣም ነው ያናደደው።
Dr. Thürmann: ትሁርማን፣ ዶር/ትሁርማን - አንተስ ማነህ?
Andreas: እኔ እንግዳ ተቀባዩ ነኝ
Dr. Thürmann: ማን ትባላለህ?
Andreas: አንድሬያስ ሼፈር
Dr. Thürmann: አሃ - ሼፈር ... ሼፈር ..... ደህና ......

ኢክስ ትህትና በጎደለው ሁኔታ du ስትል ዘወትራዊውን የአጠራር መልክ በመጠቀም ዶር/ትሁርማንን ትጠይቃለች።
Ex: አንተስ ማነህ?
Dr. Thürmann: (በመናደድ) አንተ? አንቺስ ማነሽ? ሀም.........
Andreas: ይቅርታ! ይቅርታ!

## ምእራፍ 5
## ይህ ትህትና የጎደለው ነገር ነው!

ዶር/ትሁርማን አንድ ቢራ ያዛል። አንድሬያስም ይህንኑ ወደ ክፍሉ ይወስድለታል። ዶር/ትሁርማን ዘወትራዊ በሆነ መልክ du ተብሎ

በመጠራቱ ሳይገረም አልቀረም። ነገሩ ትህትና የጎደለው መሆኑንም ጊዜ ሳይፈጅ ወዲያው ለአንድሬያስ ያስረዳል። (በመጀመሪያ አንድሬያስ የዶር/ትሁርማንን ክፍል በር ይቆረቁራል)

| | |
|---|---|
| Dr. Thürmann: | አቤት? ግባ! |
| Andreas: | ይሄው ቢራዎ |
| Dr. Thürmann: | አመሰግናለሁ፤ አንተ እንግዳ ተቀባዩ ነህ - አይደል? |
| Andreas: | አዎን |
| Dr. Thürmann: | ደህና፣ እኔ ..... እኔ በጣም ገርሞኛል። ለምንድነው du (አንተ) ብለህ የምትጠራኝ? |
| Andreas: | ማን? እኔ? |
| Dr. Thürmann: | የለም! የለም! የለም! ይህ ትህትና የጎደለው ነገር ነው፣ ወጣት ሰው! |
| Andreas: | አዝናለሁ፣ እባክዎን ይቅር ይበሉኝ |

ዶር/ትሁርማን በከፊል ፌዝ በተመላበት መንፈስ አንድሬያስን ቀልደኛ ቢጤ ትመስላለህ ይለዋል። ከዚያም ደክሞት ስለነበር ከመልካም ሌሊት ምኞት ጋር አንድሬያስን ይሰናበተዋል።

| | |
|---|---|
| Dr. Thürmann: | ቀልደኛ ቢጤ ነህ፣ አይደል? |
| Andreas: | ቀልደኛ? |
| Ex: | የለም ኮቦልድ ነኝ - እኔ ኮቦልድ ነኝ |
| Dr. Thürmann: | ይሁን ቀልደኛም ሆንክ ኮቦልድ ወይም ........ እኔ ደክሞኛል - መልካም ሌሊት! |
| Andreas: | ደህና ይደሩ ዶር/ትሁርማን |

አንድሬያስ በመጨረሻም ኤክስ ትህትና የጎደለው ድርጊት እንደፈጸመች ለመግለጽ እድል ያገኛል።

| | |
|---|---|
| Andreas: | ኤክስ? ኤክስ? |
| Ex: | አቤት? ምነው? |
| Andreas: | ደህና ...... ትህትና የጎደለሽ ነሽ |
| Ex: | እኔ? ትህትና የጎደለኝ? |
| Andreas: | አዎን አንቺ! |
| Ex: | አዝናለሁ እኔ .......... |
| Andreas: | «እና አንተስ ማነህ?» ብሎ መጠየቅ ትህትና የጎደለው ነገር ነው |
| Ex: | ደክሞኛል |
| Andreas: | የለም አንቺ ቀልደኛ ቢጤ ነሽ |

## ምእራፍ 6
## ምን ይሰራሉ?

ዶር/ትሁርማን አንድሬያስን ለማነጋገር ይፈልጋል። ስለዚህም ወደ ክፍሉ ብቅ እንዲል ይጠራዋል። ዶር/ትሁርማን አንድሬያስ ምን እንደሚሰራ ለማወቅ በጣም ነው ጉጉት ያደረበት። ስለዚህም ቀጥተኛ ጥያቄዎች ያቀርብለታል። አንድሬያስ የጋዜጠኝነት ሙያ ተማሪ ነው። ዘገባዎችንም ይጽፋል። ይህ ደግሞ የዶር/ትሁርማንን ትኩረት መሳቡ አልቀረም። (አንድሬያስ በር ይቆረቁራል)

| | |
|---|---|
| Dr. Thürmann: | አቤት? ግባ |
| Andreas: | እንደምን አደሩ ዶር/ትሁርማን |
| Dr. Thürmann: | እንደምን አደርክ ወጣት ሰው፣ እስቲ ንገረኝ ለመሆኑ ስራህ ምንድነው? |
| Andreas: | እማራለሁ |
| Dr. Thürmann: | ስነ ስርአት የጎደለው ተማሪነት - ለመሆኑ ምንድነው የምትማረው? |

Andreas: ጋዜጠኝነት
Dr. Thürmann: እና በትክክል ምን ታደርጋለህ?
Andreas: ነገሮችን መመርመር፣ ዘገባ መጻፍ ........
Dr. Thürmann: ትኩረትን የሚስብ - በጣም የሚስብ ነገር ነው

አንድሬያስ በሆቴል አውሮፓ የሚሰራው ለትምህርቱ የሚያስፈልገውን ወጪ የሚሸፍንበትን ገንዘብ ለማግኘት ነው።
Dr. Thürmann: እና እዚህ ምን ታደርጋለህ?
Andreas: እሰራለሁ
Dr. Thürmann: ምንድነው የምትሰራው?
Andreas: እንግዳ ተቀባይ ነኝ
Dr. Thürmann: ለስራው አዲስ ነህ - አይደል?
Andreas: አዎን
Dr. Thürmann: እንግዲህ ጋዜጠኝነት ትማራለህ - እና እዚህ ደግሞ ትሰራለህ፣ ገንዘቡ የሚያስፈልግህ መሰለኝ
Andreas: አዎን በእርግጥ
Dr. Thürmann: የሚያስገርም ነው፣ በል ደህና ሁን!
Andreas: ደህና ሁኑ ዶር/ትሁርማን

ኤክስ በበኩሏ የውይይቱን ይዘት ቤት - መት በሆነ ግጥም መልክ እንደሚከተለው ትደረድራለች።
Ex: መማር መመራመር ..... ትኩረትን የሚስብ ነው፣ በጣም ትኩረትን የሚስብ ነው

## ምእራፍ 7
## የተለየ ነገር ነሽ

አንድሬያስ የሚማረው የጋዜጠኝነት ሙያን ሲሆን ኤክስ ደግሞ ሰዎችን አጠናለሁ ትላለች። የፈጠራ ምስላችን ኤክስ የሰውልጆች ትኩረትን የሚስቡ እንደሆኑ ነው የምታምነው።
Ex: ሄላው አንድሬያስ!
Andreas: እዚህ ምን ታደርጊያለሽ?
Ex: እማራለሁ
Andreas: ምን አልሽ? እማራለሁ?
Ex: አዎን እማራለሁ
Andreas: ምንድነው የምትማሪው?
Ex: ሰዎችን
Andreas: አሃ - ሰዎችን ነው የምታጠኚው
Ex: አዎን! ጥናት አካሂዳለሁ፣ ሰዎችን አጠናለሁ
Andreas: አህ - አንቺ የተለየሽ ነገር ነሽ
Ex: ሰዎችም የተለዩ ናቸው

አንድሬያስ - ለመሆኑ የሰውልጅ ምን አይነት ፍጡር ነው? እያለ ይመራመራል። ኤክስ ግን በጉዳዩ ከአንድ ድምዳሜ ደርሳለች። ለኤክስ የሰውልጆች የተለዩ ነገሮችና ጉጉተኛ ፍጡራን ናቸው።
Andreas: ሰዎች ህም..... ሰዎች ህም.... እንዴት አይነት ፍጡራን ናቸው?
Ex: ትህትና የጎደላቸው፣ የሚደክማቸው፣ ትኩረትን የሚስቡ፣ የተለዩ ናቸው
Andreas: እንዴት አባክሽ? ምን?
Ex: ሰዎች ትህትና የጎደላቸው፣ የሚደክማቸው፣ በጣም የሚስቡ፣ የተለዩና ጉጉተኞች ናቸው

## ምእራፍ 8
## ከየት ነህ - ከየት ትመንጫለህ?

የሚከተሉት ድርጊቶች የሚፈጸሙት በሆቴል አውሮፓ የቁርስ አዳራሽ ውስጥ ነው። አንድሬያስና ኤክስ እንዴት እንደተገናኙም በዚህ ምእራፍ ትረዳላችሁ። በመጀመሪያው ድርጊት በሆቴል አውሮፓ በክፍል አጽጂነት ከምትሰራው ከሃና ከላዘን ትተዋወቃላችሁ። ሃና በትሪ ደርድራ የያዘችው እቃ ድንገት ይወድቅባታል። አንድ ቅን እንግዳም ስብርባሪውን በማንሳት ይረዳታል።

| | |
|---|---|
| **1. Frau = የመጀመሪያዋ ሴት** | **1. Mann = የመጀመሪያው ወንድ** |
| **2. Frau = ሁለተኛዋ ሴት** | **2. Mann = ሁለተኛው ወንድ** |
| **3. Frau = ሶስተኛዋ ሴት** | **3. Mann = ሶስተኛው ወንድ** |

**1. junge Frau:** እንደምን አደርሽ
**2. Junge Frau:** እንደምን አደርሽ
(በትሪ ላይ የነበረው ሰሃን፣ ሲኒ ወዘተ» ወድቆ ይከሰከሳል)
**Hanna:** ውይ! ወይ ጉዴ!
**1. Hotelgast:** አሀ - ይቆዩማ!
**Ex:** አቤት፣ ሁሉም ተሰበረ!
**Hanna:** አመሰግናለሁ፣ በጣም አመሰግናለሁ፣ በጣም ቅን ነዎት
**Ex:** በጣም ቅን ነዎት

በሁለተኛው ድርጊት ደግሞ አንድ እንቅልፉን ደህና አድርጎ ያልጨረሰ ሰው ወደ ቁርሱ አዳራሽ ይገባል።
**Hanna:** እንደምን አደሩ
**2. Hotelgast:** .... አደርሽ
**Hanna:** ሻይ ወይስ ቡና?
(ሰውየው ምንም መልስ አይሰጥም)
**Hanna:** ይቅርታ ያድርጉልኝ፣ ሻይ ነው ወይስ ቡና የሚፈልጉት?
**2. Hotelgast:** አዝናለሁ ገና በጣም እንደደከመኝ ነኝ፣ ቡና!

በሶስተኛው ድርገት ዶር/ትሁርማንና አንድ የቀድሞ ወዳጁ እናዳጋጣሚ በሆቴል አውሮፓ ይገናኛሉ። በአይን ከተያዩ ብዙ ጊዜያቸው ነው።
**1. Hotelgast:** እንደምን አደሩ
**Dr. Thürmann:** እንደምን አደሩ
**1. Hotelgast:** ማን ናቸው እኚህ ሰው? ይገርማል፣ በጣም ይገርማል፣ በእርግጥም በጣም..... ይቅርታ ያድርጉልኝ እባክዎ!
**Dr. Thürmann:** እሺ! ምንድነው እሱ?
**1. Hotelgast:** ዶር/ትሁርማን ነዎት፣ አይደሉም?
**Dr. Thürmann:** አዎን አንተስ! አንተ ....... ስቴፋን መሆን አለብህ!

በአራተኛው ድርጊት አንድ ወጣት ሰው ከአንዲት ሴት ጋር ውይይት ለመክፈት ይሞክራል። እና ብዙ ጥያቄዎችን ያቀርብላታል።
**Junger Mann:** እስቲ ይንገሩኝ! ጋዜጠኛ ነዎት እና ዘገባዎችን ይጽፋሉ ማለት ነው?
**Journalistin:** አዎን
**Junger Mann:** ይሰባል፣ በጣም ይሰባል፣ ይህ በጣም ትኩረትን የሚስብ ነው
**Journalistin:** አዎን ልክ ነው
**Junger Mann:** እስቲ ይንገሩኝ - በትክክል ምንድነው የሚያደርጉት?
**Journalistin:** አሀ - ምርምር ........
**Ex:** ምርምር፣ ምርምር ........

በአምስተኛው ድርጊት ሁለት ወጣት ሴቶች (ከነዚሁ አንዷቱ ተማሪ ናት) ከአንድ ከተማ ማለትም ከአውግስቡርግ እንደሚመነጩ ይረዳሉ። አውግስቡርግ በደቡባዊው ጀርመን ሚዩኒክ አጠገብ የምትገኝ ከተማ ናት።

1. junge Frau: አንቺስ ምን ታደርጊያለሽ?
2. junge Frau: ተማሪ፣ እኔ ተማሪ ነኝ
1. junge Frau: እና ከየት ነው የምትመነጪው?
Studentin: ከአውግስቡርግ
1. junge Frau: በሃቅ? እኔም!
Studentin: ምን? አንቺም ከአውግስቡርግ ነሽ?

ከዚያም ኤክስ አንድሬያስ ከየት እንደሚመነጭ ትጠይቀዋለች። አንድሬያስም በፊናው እየቀለደ ኤክስን አንቺስ ከየት ነሽ ይላታል።

Ex: አንድሬያስ! አንተ ከየት ነው የምትመነጨው?
Andreas: እኔ የምመነጨው ከኮሎኝ ነው።አንቺስ? ከየት ነሽ?
Ex: እኔ? እኔ የምመነጨው ........

በመጨረሻው ድርጊት ድምጽዋ በግልጽ የሚሰማ ይሁን እንጂ በአይን የማትታየው ኤክስ እንዴት ወደ አንድሬያስ እንደመጣች ትረዳላችሁ። እንዲህ ነው! አንድሬያስ Heinzelmännchen ስለሚባሉት ድንክዬ መሰል የኮሎኝ በጎ መናፍስት የሚተርት አንድ መጽሃፍ ያነባል። እፊ ታሪኩ እንደሚለው እነዚሁ በጎ መናፍስት የእጅ ጥበብ ሙያተኛው ሌት እንደተኛ ወደ ከተማው መጥተው ስራውን ሁሉ አከናውነው ይሄዱ ነበር። ስለዚህም በኮሎኝ ከተማ ነዋሪዎች ዘንድ በጣም ተወዳጅ ነበሩ ነው የሚባለው። አንድሬያስ ከእንቅልፉ እንዳንሰራራ ሰው በመንጠራራት ምነው እኔም እንዲህ ስራዬን ለመጨረስ የሚረዳኝ ባገኘሁ ይላል። ሆኖም ያ ወርቃማ ጊዜ እንዳለፈና በዚህም በዚያም (sowieso) እንደገና ተመልሶ እንደማይመጣ ለራሱ ይነግራል። በዚህ ወቅት (sowieso) የሚለውን «አስማታዊ» ቃል የሰማች አንዲት ነገር ድንገት ከመጽሃፉ እንጣጥ ብላ ትወጣለች። አንድሬያስ የፈጠራ ምስሉን ኤክስ ብሎ ይሰይማታል። Ex በላቲን ከ አንድ ነገር የወጣ ወይም የመነጨ እንደማለት ያህል ነው። አንድሬያስ በእርግጥ (sowieso) የሚለው ቃል እንዲህ አይነት ተአምር ያመጣል ብሎ አልጠበቀም።

Andreas: እኔም እንዲህ አይነቱን ..... ባልጠላሁ፣ ግን እነዚያ ጊዜያት አልፈዋል
Ex: ህም..... ህም.... ሄላው! ሄላው! እዚህ ነኝ!
Andreas: ማነሽ አንቺ?
Ex: እኔ .....
Andreas: ማነሽ አንቺ?
Ex: እኔ እኔ ነኝ

ምእራፍ 9
ታውቀዋለህ! / ታውቂዋለሽ እኮ!

ኤክስ ሲበዛ ጉጉተኛ ናት። በመሆኑም ስለ ዶር/ትሁርማን በተቻለ መጠን ብዙ ለማወቅ ትፈልጋለች። አንድሬያስና ኤክስ የዶር/ትሁርማንን ማንነት በዝርዝር ለማወቅ የሆቴሉን የእንግዳ መመዝገቢያ ያገላብጣሉ። ይህ ደግሞ ስለ ራሳቸው የመጀመሪያና ተከታይ ስሞች እንዲያወሩ መንስኤ ይሆናል።

Andreas: ይሄው እዚህ - ሁለተኛ ስም ትሁርማን
Ex: እሱን አውቀዋለሁ! ቀጥል!
Andreas: የመጀመሪያ ስም ሉካስ
Ex: የመጀመሪያ ስም?
Andreas: አዎን የመጀመሪያ ስም
Ex: ያንተ የመጀመሪያ ስም እንዴት ነው?

Andreas: እሱንማ ታውቂዋለሽ፣ አንድሬያስ! ያንቺስ የመጀመሪያ ስም ምንድነው?
Ex: አላውቀውም
Andreas: ግን እኔ! እኔ አውቀዋለሁ! የመጀመሪያ ስምሽ Ex ሁለተኛ ስምሽ Hex (ጠንቋይ) ነው
Ex: አይደለም፣ አይደለም!

ኤክስና አንድሬያስ በዚሁ ውይይታቸውን አብቅተው ወደ ዶር/ትሁርማን ይመለሳሉ። ዶር/ትሁርማን ሃኪም ነው። የተወለደው በላይፕሲግ ሲሆን የሚኖረው ደግሞ በርሊን ውስጥ ነው።
Andreas: እንቀጥል! ሙያ.......
Ex: ምንድነው የሚሰራው?
Andreas: ሃከም ነው፣ የሚጠራውም እኮ ዶር/ትሁርማን ተብሎ ነው
Ex: ያንተ ስራ ምንድነው?
Andreas: ተማሪና እንግዳ ተቀባይ ነኝ፣ እማራለሁ እንደ እንግዳ ተቀባይም እሰራለሁ
Ex: ቀጥል! የትውልድ ስፍራ! ከየት ነው የሚመነጨው?
Andreas: ከላይፕሲግ ነው የሚመነጨው
Ex: ቀጥል! የመኖሪያ ስፍራ
Andreas: ቆይ አንድ ጊዜ .... ይሄውና.... በርሊን.... በርሊን ውስጥ ነው የሚኖረው

ምእራፍ 10
የቀረ አንድ ነጻ ክፍል አለ?

አንድሬያስ በሆቴሉ የእንግዳ መቀበያ ተቀምጦ አንዳንድ የቢሮ ስራዎችን ለማጠናቀቅ እየሞከረ ነው። ኤክስ በፊናዋ የጥያቄ መአት ታወርድበታለች።
Ex: አንድሬያስ፣ አንተ ትሰራለህ?
Andreas: አዎን
Ex: አንተ - አንድሬያስ፣ ብዙ ትሰራለህ?
Andreas: አዎን
Ex: አንድሬያስ፣ ደስተኛ ነህ?
Andreas: ህም.....
Ex: ምንድነው «ህም»? ነህ ወይስ አይደለህም?
Andreas: ሁሌ እንዲህ ብዙ ትጠይቂያለሽ?
Ex: ሁሌ!
Andreas: ዝም - የሆነ ሰው እየመጣ ነው!

በዚሁ ወቅት አንድ እንግዳ ወደ ሆቴሉ ገብቶ ነጻ ክፍል እንዳለና ይሄው ምን ያህል እንደሚያስከፍልም አንድሬያስን ይጠይቃል። አዲሱ እንግዳ አቶ ማየር ሁለት ወይም ሶስት ሌሊት ለመቆየት እንደሚያስብ ጨምሮ ያስረዳል።
Andreas: እንዴት አመሹ
Gast: እንዴት አመሸህ፣ ነጻ ክፍል አለ?
Andreas: ባለአንድ ወይስ ባለሁለት አልጋ ክፍል?
Gast: ባለአንድ አልጋ ክፍል
Andreas: መታጠቢያ (ባኞ) ያለው?
Gast: አዎን
Andreas: ምን ያህል ጊዜ ይቆያሉ?
Gast: ሁለት ወይም ሶስት ሌሊት
Andreas: ደህና፣ ክፍል አስር ገና ነጻ ነው
Gast: ክፍሉ ምን ያህል ይወደዳል?
Andreas: ከቁርስ ጋር አንድ መቶ ሃያ ማርክ

Gast: መልካም
Andreas: ቁልፍዎ ይሄው - መልካም ምሽት ይሁንልዎት፣ አቶ ማየር!
Gast: አመሰግናለሁ

አቶ ማየር ሙዚቀኛ እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህንኑ ከክፍሉ ዘልቆ የሚሰማው የዋሺንት ድምጽ ያመለክታል።
Andreas: እንዴት ውብ ነው!
Ex: ጸጥታ! እባክህ ጸጥታ!

## ምእራፍ 11
## እንደገና እንዲህ አይነት ክፍል!

የሆቴል አውሮፓ ሰራተኛ የሆነችው ሃና ክፍል እያጸዳች ነው። አንድ እንግዳ ክፍሉን አዝረክርኮ በመሄዱ በጣም ተናዳለች።
Frau Berger: እንዴት አደርሽ ሃና
Hanna: እንደምን አደሩ ወሮ/በርገር፣ ምነው እቴ! ደግሞ እንደገና እንዲህ የተዝረከረከ ክፍል! እንዲህ አይነት ቆሻሻ!
Frau Berger: ምነው ሃና?
Hanna: አሀ - ይሄ ክፍል በእውነት የከብት በረት ነው!
Frau Berger: ታውቂዋለሽ እኮ (አዲስ ነገር አይደለም)
Hanna: ልክ ነው

ሃና ጠርሙሶችን ማነሳሳትና የሲጋራ መተርኮሻውን መጥረግ ትጀምራለች። ይህን እያደረገች ሳለም የሴትነትን እጣ በማንሳት ታማርራለች። ሃና ወንዶች ያጤሳሉ - ይጠጣሉ፣ ሴቶች ደግሞ በመጨረሻ ሁሉንም ያጸዳሉ ትላለች።
Hanna: የተለመደ ነው - አንዱ ጠርሙስ እዚህ ሌላው እዚያ! አሀ! ጠርሙሱ በግማሽ እንደሞላ ነው የሲጋራ መተርኮሻውም ጢም ብሏል - እርግጥ ነው፣ ምናለ ወንድ ያጤሳል ይጠጣል ሴት ትጠርጋለች
Ex: ትዘፍናለችም
Hanna: ምን? የሆነ ሰው አለ እዚያ?

በተፈጥሮዋ ጉጉቷ የሆነችው ኤክስ በሆቴሉ ውስጥ የሚደረገውን ነገር ሁሉ ትከታተላለች። ስውር ትሁን እንጂ የማታየውና የማትሰማው ነገር የለም። የሆቴሉ እንግዳ በሆነው በአቶ ማየር ላይ በማሾፍ Musikant (ሞዛቂ) ብላ ትጠራዋለች። ይህ የአንድን ሙዚቀኛ (Musiker) ሙያ የሚያቃልል አነጋገር ነው።
Frau Berger: ሁሉም ነገር ደህና፣ ሃና? አሀ! እንዲት ዋሺንት!
Ex: አንድ ሞዛቂ - ዝርክርክና የደስደስ ያለው
Hanna: የሆነ ሰው አለ እዚያ?
Frau Berger: የሆነ ሰው አለ እዚያ? ይገርማል ....

## ምእራፍ 12
## ተማሪ ወይስ እንግዳ ተቀባይ?

አንድሬያስ ኤክስን እየፈለገ ሳለ ድምጽዋን ከሃና ዘንድ ይሰማል። በዚሁ አጋጣሚም ከሃና ጋር ይተዋወቃል። አንድሬያስና ሃና ከዚህ ቀደም ተገናኝተው አያውቁም። አንድሬያስ በዚሁ ወቅት ሃና ዘንድ ምን እያደረገ እንደሆነም ለወሮ/በርገር ማስረዳት አለበት።

Frau Berger: ይገርማል
Ex: ምንድነው የሚገርመው?
Frau Berger: የሆነ ሰው አለ እዚህ?
Ex: አዎን እኛ!
Andreas: እሽ! ዝም በይ እንጂ!
Frau Berger: ምን ታደርጋለህ እዚህ?
Ex: እንማራለን
Hanna: ምን አልክ እባክህ?
Andreas: አዎን፣ የለም .... እኛ .... (በመንተባተብ) ጉጉት ስላደረብኝ ብቻ ነው
Frau Berger: ይደንቃል! እስቲ ንገረኝ፣ ብቻህን ነህ ወይስ አይደለህም? ለመሆኑ «እኛ» ብለህ ስትናገር ሁልጊዜ «እኔ» ማለትህ ነው?
Andreas: የለም፣ በእርግጥ አይደለም

አንድሬያስ እንግዳ ተቀባይና ተማሪ እንደሆነ በመግለጽ ራሱን ከሃና ያስተዋውቃል። ሃናም የሆቴሉ ክፍል አጽጂ እንደሆነች በፊናዋ ትነግረዋለች። ወሮ/በርገር ደግሞ የተደሰተች ትመስላለች።
Hanna: እዚህ አዲስ ነህ፣ አይደል? እንግዳ ተቀባዩ ትመስለኛለህ
Andreas: ልክ ነው!
Hanna: እና ለምንድነው ታዲያ «እኛ እንማራለን» የምትለው?
Andreas: እኔ ተማሪ ነኝ
Hanna: በትክክል ምን? ተማሪ ወይስ እንግዳ ተቀባይ?
Andreas: ተማሪና እንግዳ ተቀባይ
Hanna: አሃ ገባኝ፣ መልካም፣ እኔ ክፍል አጽጂዋ ሃና ነኝ
Frau Berger: በሉ እስቲ በየስራችሁ ተሰማሩ!
Hanna: እሺ፣ ደህና ሁን!
Ex: ቻዎ!

## ምእራፍ 13
## ቁልፉ ይሄውና!

የሚከተሉት ድርጊቶች የሚፈጸሙት በሆቴል አውሮፖ የእንግዳ መቀበያ ነው።
ድርጊት 1 - አቶ ማየር ቁልፉን ያስረክባል።
Andreas: እንደምን አደሩ አቶ ማየር - እንዴት ነዎት?
Herr Meier: ደህና፣ አመሰግናለሁ
(አቶ ማየር ቁልፉን በእንግዳ መቀበያው ከሚገኘው ጠረጴዛ ላይ ያኖራል)
Herr Meier: ቁልፉ - ይሄውና!
Andreas: አመሰግናለሁ፣ መልካም ቀን!
Herr Meier: ደህና ሁን!

ድርጊት 2 - አንድሬያስ ለአንዲት ሴት ፓስፖርትዋን መልሶ ይሰጣል።
Andreas: እንደምን አደሩ
Frau: እንደምን አደርክ
Andreas: ይሄው፣ ፓስፖርትዎን ይውሰዱ!
Frau: አሺ አመሰግናለሁ፣ ደህና ሁን
Andreas: ደህና ሁኑ

ድርጊት 3 - አንድሬያስ ለዶር/ትሁርማን አንድ ደብዳቤ ይሰጣል። ሆኖም ዶር/ትሁርማን መነጽሩን ፈልጎ በማጣቱ ደብዳቤውን ሊያነብ አልቻለም። ለነገሩ ግን መነጽሩን አናቱ ላይ እንደሰካ ነው።
Andreas: እንደምን አደሩ ዶር/ትሁርማን፣ እንዴት ነዎት?

Dr. Thürmann: እንዴት አደርክ፣ አመሰግናለሁ - ምንም አይል
Andreas: ይሄው አንድ ደብዳቤ መጥቶልዎታል
Dr. Thürmann: ኦህ - ደብዳቤ! መነጽሬ - መነጽሬ ጠፋብኝ!
ደብዳቤው ከየት ነው የመጣው?
Andreas: ከበርሊን ነው! ይቅርታ ያድርጉልኝ ዶር/ትሁርማን፣
መነጽርዎ እኮ ያውና!
Dr. Thürmann: እንዲህ አይነት ነገር ...... እርጅና እየተጫጫነኝ ነው

ድርጊት 4 - ኤክስ በስራው ላይ ለማተኮር የሚሞክረውን አንድሬያስን ትረብሻለች።

Ex: ህም.... ህም ...
Andreas: ይህ የኔ ብእር ነው!
Ex: ያንተ ብእር? ኦህ፣ አላወቅኩም ነበር ..... መነጽሩም
ያንተ ነው?
Andreas: አይደለም! ኤክስ ዝም በይ! እየሰረሁ እኮ ነው
Ex: መስራት፣ መስራት፣ የሰውልጆች ሁሌ ይሰራሉ ......

## ምእራፍ 14
## ወደ አኸን ትመጣላችሁ?

አንድሬያስ ለወላጆቹ ደብዳቤ እየጻፈ ነው። በሆቴል አውሮፓ ስለሚያከናውነው ስራና በዚያው ስለሚታዘባቸው ሰዎች ለምሳሌ ያህል ስለ ዶር/ትሁርማንና ስለ አቶ ማየር ያትታል።

የተወደዳችሁ ወላጆች፣
እንደምታውቁት ተማሪ ሁሌ ገንዘብ ያስፈልገዋል። እኔም እንደገና ስራ ይዣለሁ። አኸን ውስጥ በሆቴል አውሮፓ በእንግዳ ተቀባይነት እሰራለሁ። ስራው አዲስና ትኩረትን የሚስብ ነው። ሁልጊዜ አንድ ነገር የሚጠይቅ ሰው አይጠፋም። አንዱ መጥቶ ክፍል እፈልጋለሁ ይላል። ሌላው ደግሞ ቢራ እንዲቀርብለት ወይም ታክሲ ....... ይጠይቃል። «ገንዘቤ፣ ቦርሳዬ ወይም ፓስፖርቴ የታለ?» ብሎ የሚጠይቅም አለ። ሰዎች አንድ እንግዳ ተቀባይ ሁሉን ነገር ያውቃል ብለው የሚያስቡ ነው የሚመስለው። ደህና ጥናት እያካሄድኩ ነው። ሰዎችን ማጥናት ይዣለሁ። ለምሳሌ ያህል ከበርሊን የመጣው ዶር/ትሁርማን አለ። ደህና ሰው ነው። ግን ብዙ መጠየቅ ይወዳል። ከዚያም ሙዚቀኛው አቶ ማየር አለ። ማጤስና መጠጣት የሚወድ ይመስላል። እኔም በጣም ውድ ቢሆንም ቅሉ ማጤሴን እንደቀጠልኩ ነው። ያሳዝናል! ወደ አኸን ትመጣላችሁ፣ አይደል?

ኤክስ በዚህ ወቅት አንድሬያስ ጽሁፉን እንዲያቋርጥ ታደርጋለች። ኤክስ ወደ አኸን የሚመጣው ማን እንደሆነ አንድሬያስን ትጠይቃለች። አንድሬያስ በደብዳቤው ውስጥ ለምን ሳይጠቅሳት እንደቀረም ለማወቅ ትፈልጋለች።

Ex: በትክክል ማን (ማነው ወደ አኸን የሚመጣው)?
Andreas: ወላጆቼ
Ex: እኔስ? የታለ .... ኤክስ ጉዋደኛዬ ናት ብለህ የጻፍከው?
Andreas: አሃ፣ ገባኝ፣ የምትዪው .........

ኤክስ የምትፈልገው አንድሬያስ ለወላጆቹ ስለርሱዋ እንዲያወሳ ነው። አንድሬያስ ግን ይህን ለማድረግ ፈቃደኛ አይደለም።

Ex: እዎን!
Andreas: ተይ ኤክስ - ይሄ የሚሆን ነገር አይደለም
Ex: ለምንድነው የማይሆነው?

አንድሬያስ ለዚህ ጥያቄ መልስ በመስጠት ፊንታ ደብዳቤውን ጽፎ ይጨርሳል።
በቅርብ እስከምንገናኝ፣
የናንተው
አንድሬያስ

ምእራፍ 15
ካሴቶቹንም ትሸጣለህ?

አንድሬያስ ከቤቱ ሆኖ ያረጁ እቃዎቹን እየሰበሰበ ነው። እነዚሁኑ በአሮጌው እቃ «ቁንጫ» ገበያ (Flohmarkt) ለመሸጥ ይፈልጋል። በዚህ መሰሉ ገበያ ሰዎች የማይፈልጉትን አሮጌ እቃ ሁሉ ይሸጣሉ። ኤክስ ደግሞ አንድሬያስ የሚያደርገውን ትታዘባለች።

| | |
|---|---|
| **Ex:** | ለምንድነው እቃዎችህን ሁሉ አውጥተህ የሰበሰብከው? |
| **Andreas:** | እሸጣቸዋለሁ |
| **Ex:** | ምን? እሸጣቸዋለሁ? የት? |
| **Andreas:** | ነገ የአሮጌ «የቁንጫ» ገበያ ቀን ነው |
| **Ex:** | «ቁንጫ» ገበያ? «ቁንጫ» ገበያ? ቁንጫዎች ትሸጣለህ ማለት ነው? |
| **Andreas:** | አይደለም፣ የምሸጠው ....... ኤክስ ሄክስን ነው |
| **Ex:** | እምቢየው! እባክህ አትሸጠኝ! |

ኤክስ ከዚያም አንድሬያስ የሙዚቃ ሸክላዎቹንና ካሴቶቹን ጭምር ይሸጥ እንደሆን ትጠይቀዋለች። አንድሬያስ ይህን ለመፈለጉ ገና እርግጠኛ አይደለም።

| | |
|---|---|
| **Ex:** | ካሴቶቹንም ትሸጣለህ? |
| **Andreas:** | አዎን - አሮጌዎች ናቸው፣ አልሰማቸውም |
| **Ex:** | ሸክላዎቹስ? ሸክላዎቹንም ትሸጣቸዋለህ? |
| **Andreas:** | እኔ እንጃ፣ አይመስለኝም |
| **Ex:** | አዳዲሶች ናቸው? |
| **Andreas:** | የለም፣ በእርግጥ አይደሉም! |
| **Ex:** | እስቲ አንድ ሸክላ አጫውት |
| **Andreas:** | ደህና |

ምእራፍ 16
ይሞክሩ!

አንድሬያስ አሮጌ እቃዎቹን በገበያው ቦታ ደርድሮ ገዢ ይጠብቃል። የገበያውን ሰፍራ ወዲያ ወዲህ እያለች ስትቃኝ የነበረችው ወሮ/በርገር እንዳጋጣሚ ከአንድሬያስ ዘንድ ብቅ ትላለች። አንድሬያስም አንዲት ሻሽ ትገዛው ዘንድ ሊገፋፋት ይሞክራል።

| | |
|---|---|
| **Andreas:** | ጤናይስጥልኝ ወሮ/በርገር፣ እንደምን ነዎት? |
| **Frau Berger:** | ጤናይስጥልኝ፣ አመሰግናለሁ፣ ደህና ነኝ |
| **Andreas:** | ምናልባት አንድ ሻሽ ይፈልጋሉ? ይሄው - ይህን ይመልከቱ! በጣም ሺክ ያለ ነው |
| **Frau Berger:** | አልፈልግም፣ አመሰግናለሁ |
| **Andreas:** | ይሞክሩ! መስታወት ይሄውልዎት |
| **Frau Berger:** | አልፈልግም፣ በእውነት አልፈልግም፣ በጣም አመሰግናለሁ |
| **Andreas:** | አዝናለሁ |

ወሮ/በርገር በዚያው ወቅት አንድሬያስ ከሚሸጣቸው እቃዎች መካከል አንድ መጽሃፍ ታያለች። መጽሃፉ ረጅም ጊዜ ስትፈልገው የቆየ በመሆኑ

ጥቂት ሳታመነታ ልትገዛው ትወስናለች።

| | |
|---|---|
| Frau Berger: | እህ - ግሩም ነው! በትክክል ስፈልግ የነበረው መጽሃፍ ይሄ ነው! |
| Andreas: | እሰቲ! ከሃ - "Heinzelmännchen" |
| Frau Berger: | ምን ያህል ያወጣል? |
| Andreas: | አንድ ማርክ |
| Frau Berger: | ደህና፣ እወስደዋለሁ |

ሆኖም ኤክስ አንድሬያስ መጽሃፉን እንዲሸጥ አትፈልግም። ምክንያቱም ከአንድሬያስ ጋር ሊተዋወቁ የበቁት በዚህች መጽሃፍ አማካይነት በመሆኑ ነው።

| | |
|---|---|
| Ex: | የለም! ይህን መጽሃፍ አትሸጥም! |
| Frau Berger: | ምን አልክ? |
| Andreas: | እህ - ይቅርታ ያድርጉልኝ ወሮ/በርገር፣ ይህን መጽሃፍ አልሸጠውም፣ አዝናለሁ |
| Frau Berger: | ታዲያ ለምንድነው መጽሃፉ እዚህ የተቀመጠው? ተወው - ደህና ሰንብት |
| Andreas: | ኤክስ - ምነው? |
| Ex: | ይሄ እኮ ....... ይሄ እኮ የእኛ መጽሃፍ ነው፣ እወደዋለሁ |

## ምእራፍ 17
## አራት ሲኒዎች - አራት ማርክ ያወጣሉ

የሚቀጥሉት አራት ድርጊቶች የሚፈጸሙት በአሮጌ እቃው ገበያ ላይ ነው። ብዙ ሰዎች በዚህ አይነቱ ገበያ ርካሽና ያልታሰቡ አስደናቂ እቃዎችን ለማግኘት መዞር ይወዳሉ። በመጀመሪያው ድርጊት አንዲት ሴት የአንድን ሸሚዝ ዋጋ ለማስቀነስ ትከራከራለች።

| | |
|---|---|
| Junge Frau: | ሸሚዙን በእውነት ወድጄዋለሁ |
| Freundin: | እሰቲ አሳዪኝ! ህም.... ሞክሪው! አዎን ያምራል |
| Junge Frau: | ሸሚዙ ስንት ያወጣል? |
| Verkäufer: | አስራ ሁለት ማርክ |
| Junge Frau: | አስራ ሁለት ማርክ? በጣም ውድ ነው! (ከፈለግህ) ሰምንት ማርክ |
| Verkäufer: | በሉ አስራ አንድ ማርክ |
| Junge Frau: | በአስር ማርክ እወስደዋለሁ |
| Verkäufer: | እሺ፣ አስር ማርክ |

ሁለተኛው ድርጊት የሲኒ ግዢን ይመለከታል።

| | |
|---|---|
| Junger Mann: | ሲኒዎቹ እንዴት ናቸው? |
| Freundin: | ምንም አይሉ (ለከፋ አይሰጡም) |
| Junger Mann: | አንድ ሲኒ ምን ያህል ያወጣል? |
| Verkäufer: | አንድ ሲኒ አንድ ከሃምሳ፣ ሁለት ሲኒዎች ሁለት ማርክ |
| Junger Mann: | አራት ሲኒዎች እወስዳለሁ |
| Verkäufer: | አራት ሲኒዎች - አራት ማርክ ያወጣሉ |

በሶስተኛው ድርጊት አንድ ህጻን እናቱ ጠፍታበት ያለቅሳል። ይህን የታዘበች አንዲት ሴትም በማፈላለግ ትረዳዋለች። (Kind = ህጻን)

| | |
|---|---|
| Kind: | እማማ! እማማ! እማዬ፣ የት ነሽ? |
| Frau: | የት ናት እናትህ? |
| Kind: | አላውቅም (እኔ እንጃ) |
| Frau: | ና እንፈልጋት |

በአራተኛው ድርጊት ኤክስ አንድ የአጸድ ድንክዬ ምስል (Gartenzwerg) ታገኛለች። በመጀመሪያ የርሱዋው ቢጤ የሃሳብ ፍጡር (ኮቦልድ) ነው የመሰላት።

Ex: አንድሬያስ፣ ተመልከት አንድ ኮቦልድ
Andreas: አይደለም ኤክስ፣ የአጸድ ድንክዬ ነው
Ex: እንዴት አባክህ!
Andreas: ታውቂያለሽ ጀርመኖች የአጸድ ድንክዬዎችን እንደሚወዱ
Ex: እኔም፣ አባክህ እኔም እፈልጋለሁ...

## ምእራፍ 18
## ምንም ሻንጣ - ምንም እቃ

ጊዜው ማለዳ ነው። የሳምንቱ መጨረሻ ስላለፈ አንድሬያስ ወደ ሆቴል አውሮፓ ተመልሶ መሄድ አለበት። ወደ ስራ ለመሄድ በመቻኮሉም ቁርሱን በፍጥነት ይበላል። ኤክስ ግን ከአንድሬያስ ጋር አብራ ለመሄድ አልፈለገችም።

Andreas: ኤክስ! እኔ አሁን መሄዴ ነው፣ ትመጫለሽ?
Ex: ፍላጎት የለኝም
Andreas: ደህና - አንቺ ፍላጎት የለሽም እኔም ጊዜ የለኝም! ስለዚህ ከቤት ቅሪ! ደህና ሁኝ!
Ex: አንድሬያስ! አባክህ ጠብቀኝ፣ መጣሁ

በሆቴል አውሮፓ ክፍል አጽጂዋ ሃና አንድሬያስን ተደናግጣ ትጠብቀዋለች። ሃና በሆነ ነገር ተበሳጭታለች። አቶ ማየር ሂሳቡን ሳይከፍል ሆቴሉን ለቆ የሄደ ይመስላል።

Hanna: አንድሬያስ! ና እስቲ በፍጥነት!
Andreas: ምን ተፈጠረ?
Hanna: አቶ ማየር ጠፋ!
Andreas: ምን?
Hanna: አልከፈለም! ና ቶሎ!

ሃና የአቶ ማየርን ክፍል ለአንድሬያስ ታሳየዋለች። አቶ ማየር ከዋሺንቱ በስተቀር የተወው እቃ የለም። ሃናና አንድሬያስ ወደ አለቃቸው ሄደው ጉዳዩን ለማሳወቅ ይወስናሉ።

Hanna: ተመልከት! ክፍሉ ባዶ ነው፣ ምንም እቃ - ምንም ሻንጣ የለም
Andreas: ባኞ ቤቱም ባዶ ነው፣ የጺም መላጫ የለም - የጥርስ ብሩሽ የለም
Hanna: እርሱ ጠፍቶ አምልጧል!
Andreas: እኔ ይህን አላምንም! ተመልከች! ዋሺንቱ አሁንም እንዳለች ነው!
Hanna: እና አሁን ምን ..... ? ሃሳብ አለህ?
Ex: ጊዜ ከወሰዱ መፍትሄው አይገድም (ጊዜ ይፈታዋል)
Andreas: አለቃይቱ ነገሩን ታውቃለች?
Hanna: የለም (አታውቅም)
Andreas: ነይ እንጠይቃት

## ምእራፍ 19
## መተኛት እፈልጋለሁ

ሃናና አንድሬያስ አቶ ማየር ሂሳቡን ሳይከፍል ለቆ እንደሄደ ለሆቴሉ ሃላፊ ለወሮ/በርገር ያስረዳሉ። ሶስቱም ምን ነካው? ብለው ላንዳፍታ ማሰባቸው አልቀረም። ወሮ/በርገር በበኩሏ አቶ ማየር ሲበዛ ግድየለሽ

መሆኑን በማሰብ ምንም መጨነቅ አያስፈልግም ትላለች። ሃና ግን አቶ ማየር ጨርሶ ላይመለስ ለቆ እንደሄደ ነው የምታምነው። አንድሬያስ በፊናው አቶ ማየር ዋሺንቱን ለመፈለግ ተመልሶ እንደሚመጣ እርግጠኛ ነው።

**Frau Berger:** እባካችሁ አትጨነቁ! አቶ ማየር ሙዚቀኛ እንደሆነ ታውቃላችሁ፣ በመጠኑም ቢሆን ግድየለሽ ነው
**Hanna:** እርሱ ኮብልሏል! ለሁልጊዜ
**Andreas:** ግን ዋሺንቱ እኮ እዚህ ናት!
**Frau Berger:** አሃ .....
**Andreas:** በእርግጥ ሳይፈልጋት አይቀርም
**Frau Berger:** በትክክል! እንዲህ አይነት ዋሺንት በጣም ውድ ነው፣ እርግጥ ተመልሶ ይመጣል
**Ex:** በዚህም በዚያም
**Frau Berger:** እውን? እሺ፣ እስቲ ትንሽ እንጠብቅ
**Andreas:** መልካም

አቶ ማየር በእውነትም በዚያው ምሽት ወደ ሆቴሉ ተመልሶ ይመጣል። በጣም ደክሞታል።
**Ex:** ተመልከት! ያውና አቶ ማየር መጣ!
**Andreas:** እግዜር ምስጋና ይግባው!
**Ex:** ምናልባት አሁን ሊከፍል ፈልጎ ይሆን?
**Andreas:** እሽ - ኢክስ - እሽ (ዝም)
እንዴት አመሹ አቶ ማየር፣ ደህና ነዎት?
**Herr Meier:** ደህና አይደለሁም! በጣም ደክሞኛል፣ መተኛት ነው የምፈልገው ለአንድ ተጨማሪ ሌሊት መቆየት እፈልጋለሁ፣ ይቻላል?
**Andreas:** አንድ ጊዜ ይጠብቁ! ..... አዎን
**Herr Meier:** እግዜር ምስጋና ይግባው! ሌላ ነገር ደግሞ ዋሺንቴ... ዋሺንቴ አለች?
**Andreas:** አዎን - ዋሺንትዎ ወሮ/በርገር ዘንድ ናት
**Herr Meier:** እግዜር ምስጋና ይግባው!
**Andreas:** በሉ እንግዲህ ...... መልካም እንቅልፍ
**Herr Meier:** አህ - አመሰግናለሁ፣ አመሰግናለሁ!
**Ex:** እና መቼ ነው የሚከፍለው?
**Andreas:** እሽ - ኢክስ!

## ምእራፍ 20
## ታመዋል እንዴ?

ወሮ/በርገር ከአቶ ማየር ለመነጋገር ወደርሱ ትሄዳለች። አሞት አልጋ ላይ እንዳለም ታገኘዋለች።
(ወሮ/በርገር የክፍሉን በር ትቆረቁራለች)
**Frau Berger:** አቶ ማየር? አቶ ማየር፣ አሉ ወይ? አቶ ማየር?
**Herr Meier:** አዎን
(ወሮ/በርገር ክፍሉ ውስጥ ትገባለች)
**Frau Berger:** ምነው አቶ ማየር፣ ታመዋል እንዴ?
**Herr Meier:** አዎን
**Frau Berger:** ያሰቃይዎታል?
**Herr Meier:** አዎን፣ አዎን
**Frau Berger:** የት ላይ ነው ህመም የሚሰማዎት?
**Herr Meier:** ሁሉም ቦታ፣ ሁለንተናዬን ነው የሚያመኝ
**Frau Berger:** ትኩሳት የያዘዎት ይመስላል፣ አንድ ጊዜ! አሁኑኑ ተመልሼ እመጣለሁ

ዶር/ትሁርማን ሃኪም መሆኑን ታውቃላችሁ። በመሆኑም አቶ ማየርን መርምሮ ጉንፋን (ኢንፍሉዌንዛ) እንደያዘው ያረጋግጣል።
Dr. Thürmann: እሺ አቶ ማየር፣ እንዴት ይሰማዎታል?
Herr Meier: መጥፎ፣ በእውነት መጥፎ
Dr. Thürmann: ምንዎን ነው የሚያምዎት?
Herr Meier: ራሴን፣ አይኖቼን፣ ጉሮሮዬን፣ ሁሉም ቦታ ያመኛል

(ዶር/ትሁርማን አቶ ማየርን እየደባበሰ ይመረምራል)
Dr. Thürmann: እዚህ ላይ ያማል?
Herr Meier: አዎን
Dr. Thürmann: እዚህስ ያማል?
Herr Meier: የለም፣ ግን እግሮቼ ..... እግሮቼ በጣም ከብደውኛል
Dr. Thürmann: ደህና፣ ጉንፋን ነው የያዘዎት፣ እስከዚህ ክፉ ነገር አይደለም
Herr Meier: እግዜር ምስጋና ይግባው!
Dr. Thürmann: ምህረቱን ይላክልዎ፣ አቶ ማየር!
Herr Meier: አመሰግናለሁ! በጣም አመሰግናለሁ!

## ምእራፍ 21
## ኤሰን ነበርኩ

ወሮ/በርገር ከህመሙ ያገገመውን አቶ ማየርን በሆቴሉ የቁርስ አዳራሽ ውስጥ አግኝታ ታነጋግራለች።
Frau Berger: እንደምን አደሩ አቶ ማየር፣ ተሻለዎት?
Herr Meier: አዎን አመሰግናለሁ፣ እግዜር ይመስገን!
Frau Berger: መልካም፣ በነገራችን ላይ ዋሺንትዎ አሁንም እኔ ዘንድ ናት
Herr Meier: አዎን፣ አውቃለሁ
Frau Berger: ወደ እኔ ቢሮ እንሂድ! ዋሺንትዎም ያለችው እዚያ ነው
Herr Meier: እሺ፣ በደስታ

ወሮ/በርገር ሆን ብላ ውይይቱ ወደ አቶ ማየር መጥፋት ጉዳይ እንዲያዘነብል ታደርጋለች። አቶ ማየርም ይቅርታ በመጠየቅ ሂሳቡን ወዲያው እንደሚከፍል ይገልጻል።
Frau Berger: ያውቃሉ - ሁኔታው የሚያስገርም ነበር! ክፍልዎ ባዶ ነበር፣ ንብረትዎ በሙሉ የለም፣ እርስዎም ሄደዋል
Herr Meier: እና አልከፈልኩም! ችግርዎ ይገባኛል
Frau Berger: እንዲህ ከሆነ እንግዲያው መልካም ነው
Herr Meier: ይቅርታ ያድርጉልኝ እባክዎ! አሁኑኑ እከፍላለሁ

በእርግጥ አቶ ማየር የጠፋበትን ሁኔታ በትክክል ለማስረዳት ይፈልጋል። ኤሰን ውስጥ የምትገኝ ሴት ወዳጁን ጎብኝቶ ነበር። በዚሁ ጊዜ ደግሞ በመሃከላቸው ጥል ሳይፈጠር አልቀረም።
Herr Meier: ደህና - እዚህ አኸን ውስጥ ነበርኩ
Frau Berger: አዎን፣ አውቃለሁ
Herr Meier: አኸን ውስጥ የሙዚቃ ትርኢት ነበረብኝ
Frau Berger: አህ - የሚስብ (የሚማርክ) ነገር ነው
Herr Meier: እና ከዚያም ኤሰን ውስጥ ነበርኩ
Frau Berger: ኤሰን ውስጥ ነበሩ?
Herr Meier: አዎን ሴት ወዳጄ የምትኖረው እዚያ ነው፣ ግን ተጣልተን ነበር
Frau Berger: እርስዎም ችግር ነበረብዎት ማለት ነው
Herr Meier: እንዴታ! ከዚያም ወደ አኸን ተመለስኩ

ኤክስ ደግሞ በተለመደ የግጥም ዘዬዋ በአቶ ማየር ላይ ያላትን አስተያየት እንደሚከተለው ትደረድራለች።
Ex: አንድ ጊዜ አንድ ሙዚቀኛ ነበር፣ ዝርክርክና የደስደስ የነበረው

ምእራፍ 22
እና ሚስቱስ?

ሁለት ወይዛዝርት በሆቴል አውሮፓ የእንግዳ መቀበያ አዳራሽ ተቀምጠው አላፊ አግዳሚውን ማማት ይዘዋል። በመጀመሪያ ስለ ዶር/ትሁርማን ይነጋገራሉ።

Frau Müller: ያ ነው እርሱ!
Frau Hoffmann: አቶ ትሁርማን?
Frau Müller: አዎን
Frau Hoffmann: በእውነት ደስ ይላል! እና ሙያውስ?
Frau Müller: ዶግ፣ ይሰሙ! እርሱ ፕሮፌሰር ነው
Frau Hoffmann: አሀ - ፕሮፌሰር! ከየት ነው የመጣው?
Frau Müller: ከበርሊን
Frau Hoffmann: ሁሉን አውቃለሁ እናዳይሉኝ!
Frau Müller: አዎን፣ ደህና .......
Frau Hoffmann: እና ሚስቱስ? ማለቴ ያገባ ነው ወይ?
Frau Müller: አላውቅም፣ ግን ያገባ ነው ብዬ አላስብም

ዶር/ትሁርማን በሁለቱ ወይዛዝርት አጠገብ ሲያልፍ ሰላምታ ይሰጣቸዋል።

Dr. Thürmann: ጤናይስጥልኝ ወይዛዝርት
Frau Müller: ጤናይስጥልኝ ፕሮፌሰር ትሁርማን
Frau Hoffmann: ጤናይስጥልኝ ፕሮፌሰር ትሁርማን

ሁለቱ ወይዛዝርት ከዚያም ስለ አንዲት ሴት ይወያያሉ። ሴትዮዋ ፈረንሳዊት ናት።

Frau Müller: ያቺ ናት እርሱዋ!
Frau Hoffmann: ማን?
Frau Müller: ክፍል አስራ ሁለት ውስጥ የምትኖረው ወጣት ሴት
Französin: እንደምን አደራችሁ፣ መልካም ጠዋት!
Frau Müller: እንደምን አደርሽ ............. ፈረንሳዊት ናት
Frau Hoffmann: እሱንማ ሰማሁ እኮ!
Frau Müller: እናቲቱ ፈረንሳዊት ናት
Frau Hoffmann: አትሉኝም! አባትዬውስ?
Frau Müller: እርሱ ጀርመናዊ ነው! ዲፕሎማት
Frau Hoffmann: በጣም ያስደንቃል! እርሱዋስ ምን ታደርጋለች? ማለቴ ስራዋ ምንድነው?
Frau Müller: እንጃ፣ አላውቅም - ምናልባት ተማሪ?
Frau Hoffmann: ህም
Frau Müller: አሀ፣ ይመልከቱ .......

ኤክስ ደግሞ ሁለቱን ሴቶች Duett (ጥንድ) ብላ በመሰየም የበኩሏን አስተያየት በተለመደ የግጥም ዘዬዋ ትደረድራለች።
Ex: ጥንዱ - ይሆናል በሚል ያወራሉ - ደስ ሲሉ!

ምእራፍ 23
ማነው እዚያ የሚናገረው?

አንድሬያስ አንድ መጽሃፍ እያነበበ ነው። ኤክስ በበኩሏ ምን ታደርጋለህ? ስትል በመጠየቅ አንድሬያስን እንዳያነብ ትረብሸዋለች። አንድሬያስ የማደርገውን ታያለሽ እኮ ሲል ይመልሳል። ኤክስ ደግሞ በዚሁ በመናደድ ጨርሶ ምንም ነገር እንደማታይና እርስዋም እንደማትታይ ትናገራለች።

Ex: አንድሬያስ፣ ምን እያደረግህ ነው?
Andreas: አነባለሁ
Ex: ምንድነው የምታነበው?
Andreas: መጽሃፍ ነው የማነበው፣ ታያለሽ እኮ!
Ex: ምንም አላይም፣ ጨርሶ ምንም አላይም! እኔ አልታይም፣ ምንም ነገር ማየትም አልችልም
Andreas: ኤክስ ምንም ነገር አታይም፣ ግን ብዙ ትረብሻለች

ኤክስ ኃላ ባለ ድምጽ ራበኝ ስትል ትናገራለች። ወሮ/በርገርም ይህን ትሰማለች። ይህ የተለየ ድምጽ (የኢክስ ድምጽ) ከየት እንደሚመጣ ለማወቅ ሁሌም ስትፈልግ ነው የቆየችው። ስለሆነም ከአንድሬያስ ጋር ምግብ - ቤት ለመሄድ ትስማማለች። አንድሬያስ ደግሞ መጽሃፉን ጨርሶ ያነባል።

Andreas: ያው፣ አለቀ!
Ex: እህ! እህ! ሆዴን አመመኝ
Andreas: ኤክስ፣ ምነው?
Ex: ራበኝ!
Andreas: ኤክስን ራባት?
Ex: በዚህም በዚያም፣ እንደራበኝ ግልጽ ነው
Frau Berger: ኤኔም ርቦኛል
Andreas: እንዴት አመሹ፣ ወሮ/በርገር!
Ex: ምግብ ለመብላት አብረን እንሂድ?
Frau Berger: ጥሩ ሃሳብ ነው! ግን ንገረኝ፣ ማነው የሚያወራው? እኔ የማየው አንተን ብቻ ነው
Andreas: እኔ እኮ በሆድ መናገር እችላለሁ
Frau Berger: ገባኝ! የሚያስደንቅ ነው!
Andreas: ግን - ይህ የግል ሚስጥሬ ነው
Ex: በሉ እንሂድ!

ምእራፍ 24
ተጨማሪ ቡና ይፈልጋሉ?

ጀርመን ውስጥ ብዙ ሰዎች በፒትሴሪያዎች መመገብ ይወዳሉ። በነዚህ አይነቶቹ የጣሊያን ምግብ ቤቶች ምግቡ ጥሩ ከመሆኑም በላይ ዋጋው ያን ያህል ውድ አይደለም። ወሮ/በርገር፣ ኤክስና አንድሬያስም ባአንድ ፒትሴሪያ ውስጥ ይገኛሉ። ወሮ/በርገር ሰላጣና አሳ ለማዘዝ ትሻለች። አንድሬያስ በበኩሉ ፒትሳ ነው የሚፈልገው።

Andreas: ምን ለመብላት ይፈልጋሉ?
Frau Berger: በመጀመሪያ ሰላጣ፣ ከዚያም ..... እና ከዚያም ....... እና ከዚያም ..... አሳ! እና አንተስ? አንተ ምንድነው የምትፈልገው?
Andreas: ፒትሳ - በአሳማ ስጋ፣ በአይብና በቲማቲም
Ex: ይህን ያህል ብዙ?
Frau Berger: መጣች እንደገና - ሁለተኛ ድምጽህ!
Andreas: አዎን፣ ሲበዛ ረባሽ ናት

ቀጥለውም መጠጣት የሚፈልጉትን ነገር ይመርጣሉ።

Andreas: እሺ፣ ምን መጠጣት ይፈልጋሉ?
Frau Berger: የማእድን (ሚነራል) ውሃ! አንተስ?
Andreas: ቢራ
Frau Berger: እና ሁለተኛ ድምጽህስ?
Ex: የብርቱካን ጭማቂ
Andreas: ዝም በይ!
Frau Berger: በጥባጭ ነገር ትመስላለች ...... ሁለተኛ ድምጽህ
Andreas: ደህና፣ እንግዲህ ልዘዝ!

አንድሬያስ ቦዩ ሂሳቡን እንዲያቀርብለት ይጠይቃል። ጀርመን ውስጥ አብረው የሚመገቡ ሰዎች በተናጠል ሂሳብ መጠየቃቸው የተለመደ ነገር ነው። እያንዳንዱ ሰው የራሱን ሂሳብ ነጥሎ ሊከፍል ይችላል። ወሮ/በርገርም ራሱዋ ላዘዘችው ምግብ ነው መክፈል የምትፈልገው።

Andreas: ተጨማሪ ቡና ይፈልጋሉ?
Frau Berger: የለም፣ አመሰግናለሁ
Andreas: እንግዲያው፣ ቦይ! ሂሳብ እባክህ!
Ober: እሺ መጣሁ! ባንድላይ ወይስ በተናጠል?
Andreas: ባንድላይ
Frau Berger: የለም በተናጠል (ወደ አንድሬያስ ዞር በማለት) አንተ እኮ በዙ ገንዘብ የለህም

ምእራፍ 25
የተቀረውን እኔ እከፍላለሁ

ወሮ/በርገር፣ አንድሬያስና ኤክስ በፒትሴሪያው ተመግበው እንዳበቁ ወሮ/በርገር ለበላችውና ለጠጣችው ሂሳብ ትከፍላለች። ለቦዩም ጉርሻ ትሰጣለች።

Ober: እርስዎ የሚከፍሉት .... ?
Frau Berger: እኔ የምከፍለው ሰላጣውን፣ አሳውንና (ሚነራል) ውሃውን ነው
Ober: እሱ በጠቅላላው ሃያ ሁለት ማርክ ከሃምሳ ነው
Frau Berger: ሃያ አምስት (አድርገው)
Ober: በጣም አመሰግናለሁ

አንድሬያስ የተቀረውን ለመክፈል ፈልጎ ሳለ ቦርሳውን መርሳቱን ይገነዘባል። (ቦዩ ወደ አንድሬያስ ዞር ይላል)

Ober: እርስዎስ?
Andreas: እኔ የተቀረውን እከፍላለሁ
Ober: አንድ ፒትሳ በአሳማ ስጋ
Andreas: አዎን፣ እና ቢራው
Ober: አስር ማርክ ከሃምሳ ይሆናል
Andreas: ቦርሳዬ! ቦርሳዬን ላገኘው አልቻልኩም! ካፖርቴ ውስጥ መሆን አለበት፣ እባክህ አንድ ጊዜ!

አንድሬያስ ቦርሳውን በከንቱ ይፈልጋል። ሆቴሉ ውስጥ ነው የረሳው። ኤክስ ደግሞ ይህን ከመጀመሪያው አንስቶ ታውቅ ነበር።

Andreas: ቦርሳዬ አንቺጋ ነው?
Ex: የለም፣ እኔጋ አይደለም
Andreas: እንዲህ አይነት ችግር! ላገኘው አልቻልኩም፣ በእውነት አንቺ ዘንድ የለም?
Ex: በእውነት የለም
Andreas: ግን - የት ነው ታዲያ ያለው?

Ex: ሆቴል ውስጥ!
Andreas: እና ታዲያ ገና አሁን ነው የምትነግሪኝ? በእውነት ከዋኪ ነገር ነሽ!
Ex: በዚህም በዚያም!

ስለዚህም ወሮ/በርገር መላውን ሂሳብ ትከፍላለች።
Frau Berger: ደህና፣ እንግዲህ ሁሉንም እኔ ልከፈል

ምእራፍ 26
እጋብዝዎታለሁ

ዶር/ትሁርማን ሆቴሉን ለቆ ከመሄዱ በፊት አንድሬያስን ወደ በርሊን ለመምጣት ፍላጎት አለህ ወይ? ሲል ይጠይቀዋል። ዶር/ትሁርማን ለአንድሬያስ የሆነ ስራ አስቦለታል።
Andreas: እንደምን አደሩ፣ ዶር/ትሁርማን
Dr. Thürmann: እንደምን አደርክ! እኔ ነገ እሄዳለሁ፣ የምታውቅ ይመስለኛል
Andreas: አዎን፣ በእርግጥ
Dr. Thürmann: አንድ የምጠይቅህ ነገር አለ፣ ወደ በርሊን ለመምጣት ትፈልጋለህ?
Andreas: ምን አሉ?
Dr. Thürmann: ለአንተ የሚሆን አንድ ስራ አለኝ፣ በእርግጥ ጉዞው የእኔ ግብዣ ነው

አንድሬያስ ሳያስበው ባጋጠመው ሁኔታ ከመገረሙ የተነሳ ስለ ጉዳዩ የበለጠ ለማወቅ ፍላጎት ያድርበታል።
Andreas: ግብዣዎ ድንገት በመምጣቱ በጣም አስደንቆኛል
Dr. Thürmann: እንደምታውቀው፣ በርሊን ትኩረትን የምትስብ ናት
Andreas: እርግጥ ነው ......... እና ለእኔ የሚሆን ስራ አለዎት?
Dr. Thürmann: አዎን፣ እኔ የምፈልገው ..........
Andreas: ህም
Dr. Thürmann: እንደገና አስብበት! የስልክ ቁጥሬ ይሄውልህ፣ በርሊን ደውልልኝ
Andreas: መልካም፣ እደውላለሁ

ኤክስም በእርግጥ አንድሬያስን ተከትላ ወደ በርሊን ለመሄድ ትፈልጋለች።
Ex: እኔ አብሬህ እመጣለሁ
Andreas: አብረሺኝ ለመምጣት ትፈልጊያለሽ?
Ex: አዎን፣ እባክህ! እባክህ!
Andreas: አስብበታለሁ (እናያለን)
Ex: ታስታውሳለህ?

(ኤክስ ዶር/ትሁርማንን መስላ ለመናገር ትሞክራለች)
Ex: ትኩረትን ይስባል፣ በጣም ትኩረትን ይስባል
Andreas: ልክ ነው! በጣም ትክክል ነው!